አብሸር ወንድሜ

የሰው ልጅ ብቻዉን አንድ ሰው ነው፤ ከሰው ጋር ሲሆን ግን ብዙ ነው። የአያም ልጅ ሁሉ በአንድም ይሁን በሁለት መልኩ ድጋፍ ፈላጊ ነው። አብሸር የሚለዉን ሰው አጥብቆ ይፈልጋል። ሰው አይዘህ አትስጋ፣ የሚሆነዉን ሁሉ አብረን እንሆናለን ባይ ወንድም አስኪያገኝ ድረስ ዱንያ ከወዲህ ወዲያ የምታላጋው ግዑዝ ነው። ብቻዉን የሚንቀሳቀስ ባተሌ ነው።

መልካም ወንድም ከአላህ የተሠጠ መልካም ሀብት ነው። መልካም ወንድም ለወንድሙ አለሁልህ ይለዋል። ሀሳብ ሲገባው ምን ሆንክ ብሎ ይጠይቀዋል፣ ሲወድቅ ያነሳዋል፣ ሲሰበር ይጠግንዋል፣ ሲደክም ይደግፈዋል፣ ሲደነግጥ ያረጋጋዋል፣ ሲጠፋ ይዘይረዋል፣ በዲኑ ጉዳይ ያስታዉሰዋል፣ በዱንያ ላይ ይመክረዋል። ወንድምህ ነኝ አይዞህ! አህትህ ነኝ ከጎንህ አለሁ .. የሚል ወንድም አህት ማግኘት መታደል ነው።

ወንድም አላህ የሚልከው ሪዝቅ ነው፤ አህት ከአላህ የተላከች ፀጋ ናት። መልካም ወንድም ወይም አህት የተሠጠ ሰው ብዙ ነገር ተሠጥቷልና ስለዚሁ ጉዳይ አላህን አብዝቶ ያመሰግን። የሆድህን የምታወራው፣ ሚስጢርህን የምታካፍለው፣ ዓላማህን የምትነግረው፣ አብሮህ የሚያነባ፣ ሐዘንህን የሚረዳ፣ ጉዳትህን የሚካፈል፣ ሳትናገር የሚያነብህ፣ ቃል ሳታወጣ የሚያደምጥህ፣ ሳትተነፍስ የሚገነዘብህ ወንድም አህት ማግኘት መታደል ነው። ወንድምነት ምላስ አይደለም ተግባር ነው፤ አህትነት ወሬ አይደል ለቋም ነው፣ ወዳጅነት ልፈፋ አይደለም ድርጊት ነው። ሰዎች ባገለሉህ ጊዜ ያቀረበህ፣ በከፋህ ጊዜ ምን ሆንክ ያለህ፣ ሥምህን ሲያጠፉ የተከላከለልህ ... እሱ ነው ወንድም ማለት።

ወንድም ማለት እንደ አቡበከር ነው። የነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. ሚስጢረኛቸው ነበር። በመልዕክተኛነታቸው በመጀመርያ ያመነባቸው እርሱ ነበር። አውነተኛ መሆናቸዉን በርግጠኝነት ይመሰክር ነበር። ቁረይሾች ሲመታቸው ለርሣቸው ብሎ ተደብድቧል። በሰደት ጊዜ ባልደረባቸው ሆኖ መዲና ዘልቋል። አማካሪያቸው ነበር። ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር ሲቸግራቸው ያግዛቸው ነበር። ወንድም ማለት እንዲህ ነው። በአስፈላጊ ቦታ ላይ ሁሉ ቀድሞ የሚገኝ። ሰው ያሳለፋቸዉን ከባባድ ቁናት ሊረሳ ይችላል፤ እነዚያን ከባባድ ቁናት እንዲያልፍ ያደረጉትን ወንድም አህቶች ግን ፈጽሞ አይረሳም።

ሰባሐል ኸይር ወዳጆቼ! አላህ መልካም ወንድም አህት ይለግችሣሁ።

እያረፍን...

➢ ለማስታወስ ያህል በ1980 የተመለሳችሁ በዕድሜ 36 ዘልታችኻል። ግና አንድ ፍሬ ልጅ ነኝ አትበሉ።

➢ ዘመኑ ለማስተማርም ደዕዋ ለማድረግም መንገዱ ሁሉ የገራበት ነው። በምደር ላይ የምትኖሩት እንድ ጊዜ ብቻ ነዉና መልካም ጽፋችሁ እና ተናግራችሁ አለፉ። ሲታልፉም ለሻራችሁ ይቀራል።

➢ ነገሮችን ከአዕምሯችን ይልቅ በቀልባችን እያየን ተቸገርን። ከመጀመርያው ጀምሮ ትከከለኛዉን እይታ አላህ ይስጠን። ዐይናችን አንድ ነው እይታችን ግን የተለያየ።

➢ ያለፈው ዕድሜህ በምንም ይሁን በምን አለፈ። ተማርበት እንጂ ስላለፈው ዕድሜህ አትብሰከሰክ፤ ያለህበትን ዘመንህን በርታና ሥራበት፤ ስለወደፊቱም ቢሆን አትፍራ አላህ አለልህ።

➢ ለአላህ ብሎ የተጀመረ ነገር ፅኑ ነው፤ በጥሩ ኒያ የተፃፈ ነገር አላህ ዘንድ ተወዳጅ ነው፤

➢ ያለፈዉም፤ ያለህበትም፤ የወደፊቱም ዘመን ሁሉ የአላህ ነው።

➢ ሁሌም ጉዳያችሁን ሁሉ ለአላህ ስጡና ተኙ እሺ። ችግራችሁ ተፈቶ ይነጋል ኢንሻአላህ።

➢ ከሕይወት ተስፋ አንድንቆርጥ ሊያደርገን የሚገባ ምንም ነገር መኖር የለበትም፤ ሐዘን ከሆን መታገስ ነው፤ ሞት ከሆነ ሁላችንም ወደዚያው ነን።

➢ ለሰው ስናዝን እዝነታችንም በልኩ ቢሆን መልካም ነው። ለሰው ብለን የምናደርጋቸው የተጋነኑ መልካም ነገሮች ያልሆነ ትርጉም ሊያሠጡንና በይሉኝታ አሰረው ኃጢአት ላይ ሁሉ ሊጥሉን ይችላል።

➢ ተከበናል እኮ ጎበዝ ። ቀን ስንሸሸው የዋልነው ሁሉ ማታ ትራስ ላይ መጥቶ ይከበናል። በአላህ ተመኩና ጉዳያችሁን አራግፋችሁ ተኙ።

➢ ከሰዉም ከሱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖርህ የማይገባ ሰው አለ።

ሰባሐል ኸይር!

ወደ አላህ መሄድ ...

"ወደ አላህ እንዴት ልሂድ" ብሎ ጠየቀኝ:: በዚህ መልኩ ነው መሄድ ያለብህ ብዬ አልመከርህም:: ብቻ ወደርሱ ከመሄድ ሊታመንታ፤ ወደርሱ ከመጓዝ አትቀር:: ብቻ እንዴትም ብለህ ሂድ:: ስትፈልግ በአንፋቅቅ ሂድ:: ሰትፈልግ በዳዴ፤ ሲሻህ በእንብርክክ፤ ደግሞም በሩጫ ሂድ:: ብቻ ከመሄድ ወደኋላ አትበል:: ብቻ አንዳትቀር:: አይቀበለኝም ብለህ አትፍራ:: ወደ አላህ መሄድ ስኬት ነው፤ ወደርሱ አለማሰብ ግን ንፍቅና ነው::

ዐብደላህ ኢብኑ መከቱም ዐይነ ሥዉር መሆኑ ወደ አላህ መሄድ አለብኝ ብሎ ከመሄድ አላገደዉም:: በቁርጠኝነት ተነሳሳ::

ዐምር ኢብኑ አልጀሙሕ እግሩ የተጎዳ አካለ ሥንኩል ሆኖ ሳለ ለጂሃድ እወጣለሁ ብሎ ሲነሳ ልጆቹ ከለከሉት:: አርሱም ጉዳዩን ለነቢዩ ከሰሰ:: በዚህ አንካሳ እግሬ ጀነት መግባት አለብኝ ብሎ ቆረጠ:: እንደተመኘዉም በጂሃድ ላይ ሞተ::

ያን መቶ ሰዎችን የገደለዉን ሰዉዬ አስቲ አስታዉስ:: ዘጠና ዘጠኝ ሰው ገድሎ ወደ አላህ መሄድ አለብኝ፤ ወደርሱ እመለሳለሁ ብሎ አሰበ:: ስለ ጉዳዩም አንድ ሰው ጠየቀ:: ብዙም ዕውቀት ሰለሌለው መላም የለህ፤ ተሰፋ ቁረጥ አለው:: ከአላህ መጋረዱን አልወደደም:: አሱንም ገድሎ መቶ ሞላ:: ቀጥሎም አዋቂ ሰው ጠየቀ:: "ወደ አላህ ከመሄድ ምንም የሚያግድህ ነገር የለም ቀጥል" አለው:: ወደ አላህ በመሄድ ላይ አያለ መንገድ ላይ ሞተ:: ከጥፋት እየወጣ ነው የሚሉ እና ጥፋቱ ብዙ ነው ምህረት ሊደረግለት አይገባም የሚሉ መላእክት ተጣሉበት:: አላህም ጣልቃ ገባ:: ወደ አዝነቱም ወሰደው::

ሞት አፋፍ ላይ ሆነው አዛን ሲሰሙ ብድግ የሚሉ ደጋግ ሰዎችን ታሪክ አንብቤያለሁ:: ወዴት ነው ሲባሉ ወደ መስገድ ነው ወደ አላህ ነዋ ይላሉ::

ወደ አላህ የሚሄድ ሰው፤ ወደ መንገዱ የሚመለስ ሰው አላህ ዘንድ ትልቅ ከብር አለው:: አላህ ወደርሱ ተመላሾችን ይወዳል፤ በከብርም ይቀበላቸዋል:: በልዩ ሁኔታም ያስተናግዳቸዋል:: ወዳጄ ... ያላሚላሁት መስፈርት አለ ብለህ አስኪሞላልህ አትጠብቅ:: አሁኑኑ ወደ አላህ ሂድ:: አትጠራጠር:: አንድ እርምጃ ወደ አላህ ብትቀርብ ሁለት እርምጃ እንደሚቀርብህ አትጠራጠር:: ቀሰ አያልከ ወደርሱ ብትሄድ አየሮጠ ወዳንተ ይመጣል::

አንዳንዴ መጨከን ግድ ይላል ...

አንዳንድ ጊሳኔዎችን ለመወሰን ጨካኝ መሆን ግድ ይለናል። ዱንያ ላይ ሰንኖር ተወ/ ላይደለም አነ የሚጨከነነው። ካልጨከኑ የሚጠበቀው ፍሬ አይገኝም፤ ከሚታለመው ጊዜት አይደረስም። በድሎት ከድሎት አይደረስምና መጨከን ግድ ይላል። ምቾት ላይ ተሁኖ ምቾት አይመጣምና መራራ ጊሳኔ መወሰን ያስፈልጋል። ኮረኮንች ላይ ሲሄዱ ከአስፋልት መድረስ የለም። አንዳንድ ጊዜ ራሣችንን ለመቻል ከሰው መነጠል፤ ጊጤታማ ለመሆን ከአገር መራቅ፤ የኢኮኖሚ አቅማችንን ለማሳደግ ያለ አረፍት መሥራት ግዴታ ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ ዕውቀታችንን ለማሳደግ እንቅልፍ ማጣት፤ ተሻሽሎ ለመምጣት መሰደድ፤ ከድህነት ለመውጣት ብዙ መሥራት፤ ለመለወጥ መከራን መጋፈጥ፤ ለሙያገብ ሲሉ መርራብ፤ ከፍ ያለ ሰው ለመሆን መዋረድ ግድ ይላል።

አንዳንዴማ እንደገና ለመታደስ መሰበር፤ የተሻለ ነገር ለማግኘት ከታች መነሳት፤ በዘላቂነት ለመዳን መርዝ መጠጣት፤ ቆሞ ለመሄድ ብዙ መታገስ፤ ነገን ለማየት ዛሬን መቸገር፤ በእጅ ያለን ነገር ዋጋ ለማወቅ ማጣት፤ ጠንከሮ ለመውጣት መውደቅ፤ ተነፋፍቆ ለመገናኘት መለያየት፤ ሁሉ ነገር እንደማይዘልቅ ለመረዳት መደሕየት እና ሌላም ሌላም ያስፈልጋል።

ሕይወት እንዲህ ናት። መቸገር፤ መከሰር፤ መነዳት፤ መቁሰል፤ የሕይወት አካል ነው። ይበርደኛል፤ ይርበኛል፤ ይጠማኛል፤ ይቸግረኛል፤ አልቋቋምም፤ አልችልም _ እያሉ ሁሌም እትት ብትት ማለት፤ ከምቾት ከልል ዉስጥ ላለመውጣት ሰበብ መደርደር ዉድቀትን ያፋጥናል እንጂ ስኬትን አያመጣም። ትርፉም ራስን መጉዳት ነው የሚሆነው። አለመጀገን፤ አለመወሰን፤ መፍራት፤ መግደርደር፤ መጠራጠር፤ አለመጀመር ዋጋ ያስከፍላል።

ሰንደል ሲያቃጥሉት መልካም ሽቶ ወጣው፤ ብረት ሲያቀልጡት ጠነከረ፤ የረጋ ዉሃ ሳይሆን ትልቅ ማዕበል ብርቱ ዋናተኛን የሚፈጥረው፤ ጀግና በጦርነት መሃል ነው የሚወለደው። መቃጠልን፤ መቅለጥን፤ መገፋትን አትፍራ። መከራን ያሳወቀን ጦርነት ጠቀመን። ችግርን ያስለመደን ስደት ምስጋና ይገባል። ፅናትን ከነርሱ ተማርን።

ዱንያ የልፋት አገር ናት። በየቀኑ ከመኝታህ ስትነሳ መጀመርያ ላይ ማስታወስ ያለብህ ሙሉ ቀኑን ብቻ ሳይሆን ዕድሜ ልከህን ልፋት እንደሚጠብቅህ ነው።

አያረፍን ....

በሕይወት መቆየት ቀላል ነገር አይደለም ወዳጄ ...

በርግጥ ይህን መልዕክት ማንበብ ከቻልክ፣ በሕይወት አለህ፣ ትተነፍሳለህ፣ ጤነኛ ነህ፣ ሰላም ነህ፣ አዕምሮህ ልክ ነው፣ እጅህ ይሠራል፣ ዐይንህ ያያል፣ ፈደልም ቆጥረሃል ማለት ነው። ይህን ጽሑፍ ለማንበብ ራሱ ሰንት ፀጋዎች እንደሚያስፈልጉ አስተዉለሃል ግን!

አዎ ባለሙሉ ፀጋ ነህና አልሐምዱ ሊላህ በል።

****

ወዳጆቼ! የዕለቱ ተነሰቼ የምሮጥለትን ነገር እሱም ወደኔ እንዲሮጥ ሊድርገው በሉ። አላህ ካልቀደመን በሩጫችን ብቻ የሚሳካ ሀልም የለም።

****

ከዚያም ለመሰገድ ብዬ ቆምኩኝ።

" አሏሁ አከበር!" እንዳልኩ በርግጥም የዓለማት ጌታ፣ ፈጣሪዬ አሏህ ከሁሉም ነገር በላይ ታላቅ መሆኑን ተገነዘብኩ። ይህን ቃል ትርጉሙን ሳስተነተን የመጀመርያ ጊዜዬ ነው።

ጌታችን ሆይ! ሁኔታዬን ሳስተዉለው በሚባዳህ እየተጫወትኩ ሆኖ ይሠማኛል። እንደሚገባህ፣ የሚግንብባህን ያህል፣ በሚግገባህ መልኩ አላመለክንህምና ይቅር በለን። አልሰገድኩምና አንተው ሰግደሃል በለኝ።

****

ወዳጄ ... ፅናት ማለት ወደ ከፍተኛ የኢማን ደረጃ ብቻ ማደግ አይደለም። በፈተና ሳይሸረሸሩ፣ በዱንያዊ ጥቅም ሳይደለሉ፣ በብልጭልጭ ነገሮች ሳይታለሉ፣ ባሉበት የዲን ሁኔታ መጽናትም ትልቅ ፅናት ነው።

ለኔ ፅናት ማለት ካለሁበት የኢማን ደረጃ እንዳልወርድ መታገል፣ ወንጀል እንዳይበዛብኝ መከላከል፣ ደጋግ ሥራዎችን መጨመር፣ በሥነምግባር የተሻልኩ ሆኜ መገኘት ነው። መጨመርማ ድሮ ቀረ። አላህ ያፅናን።

ስለየትኛው አምላክ ነው የምታወሩት?

ጎረቤታችን አንዲት ጠንካራ ሴት ነበረች። ሙስሊም አይደለችም። አሁን ካሁን ሊደገልኝ ብላ ዐይን ዐይኑን የምታየው በሰሰት የምትወደው አንድ ልጅ ብቻ አላት። " እንዴት አፈር በልቼ እንዳሳደግኩት ብታውቁ ኖሮ" ስትል አሰማታለሁ ብዙን ጊዜ። የሆነ ቀን ያ ልጇ ድንገት ታመመባትና ዙሁር ላይ ያጣደፈው ህመም ለዐሰር ሳያደርሰው ሞተ። እናት በዐይኗ ሥር የሆነዉን ነገር ሁሉ እያየች ማመን አቃታት። ሶብር አጣች። ዐቅሏ እንዳትስት ሁሉ ሲጋን። ወደ መግሪብ ላይ አንድ ቄስ መጡ። "እጅጋየሁ አይዞሽ ታገሺ እንጂ።" አሏት። ዝም አለች፣ ደግሞ መልሳ አፈጠጠች።

"ታገሺ ነው ያሉት መምህሩ! አስቲ ምን አሉ መምህሩ ይድገሙ!" አለቻቸው።

"እንደው አግዚአብሄር ምን ይልሻል ታገሽ እንጂ" አሏት።

አምርራ ተናገረች " ስለየትኛው እግዚያብሄር ነው የሚያወሩኝ መምህሩ! ይሄ ምቀኛዉን ነው! ገና ለገና ልጇ አደገላት ብሎ አንድ ልጇን የነጠቀኝን ነው።" ብላ መምህሩን አጣደፈች። "ስለየትኛው እግዚአብሄር ነው የሚያወሩት መምህሩ! ምቀኛ አኮ ነው!"ብላ የምታምንበትን አምላክ ባንዴ ካደች። መምህሩም ሐዘን ብሥቱም ይለፍላት ብለው ነው መሰል ብዙ ሊመክሯት አልሞከሩም።

እኔ ግን አነኚህን ቃላቶች ይዤ ከድንኳኑ ወጣሁ። እግረመንገዴንም በሐዘን ጊዜ ስለሚኖረን ምላሽ ስለራሴና ስለሌሎችም ሁኔታ አሰብኩ። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) መቃብር አጠገብ ሆና ስታለቅስ ያዩዋትና "ታገሺ." ያሏት ሴት ትዝ አለችኝ። "በኔ የደረሰ መች ደረሰብህና" አለቻቸው። አላወቀቻቸዉም ነበር። ኋላ ላይ መጥታ "አላወቅኮትም እኮ" ስትላቸው። "ትከከለኛው መታገስ በመጀመርያው ድንጋጤ/ ምት ላይ ነው።" አሏት። እውነተኛ ትዕግስት ችግር አንዳገኘን ነው። ቆይቶማ ሁሉም ሳይወድ በግዱ ይታገሳል እንደማለት። በርግጥ ሐዘን ከባድ አደጋ ነው። ሐዘን እንዳገኛቸው ወዲያዉኑ የሚታገሱት የእውነተኛ ኢማን ባለቤቶች ናቸው። እየቆየ ሲሄድ ነገሮች እየተረሱ ስለሚሄዱና ተስፋ መቁረጥም ስለሚከተል ማንም ይታገሳል። ያ ትከከለኛ ትዕግስት ሊሆን አይችልም።

ሐዘን ባገኘበት ቅጽበት ወዲያዉኑ መታገስና "ኢንና ሊላህ ..." ማለት አላህ ዘንድ ያሰወድዳል። ትልቅ ምንዳን ያስገኛል፤ ከዚያም አልፎ በተሻለ ነገር ያስከሳል ወዳጄ።

የተፃፈ ቀደር ይቀየራል እንዴ

" እንዴ እንዴ የተፃፈ ቀደር ይቀየራል እንዴ?" አላቸው ደረሳው ለሸይኹ::

" እንዴ ዱዓ ቀደርን ዘወትር እንደሚታገለው ኢታውቅምን?!" አሉት ሸኾቹ::

"ቀደር" ማለት በኛ ጉዳይ አላህ ቀድሞ የወሰነው ጉዳይ ነው:: አም አንዳንድ በተከታተይትና ሳይታከቱ፣ ሳይሠለቹ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ የሚደረግ ዱዓ ከጥንካሬው የተነሳ ቀደርን ሊጥለው ሁሉ ይታረባል:: በዚህ ላይ ደግሞ ደጋግ የአላህ መላእክት ጭምር ያግዙታል:: "አላህ ሆይ የዚህን ባርያህን ዱዓ ስማ!" እያሉ አላህን ይለምኑለታል:: ወዳጄ ሆይ! ዱዓ የአላህ መሻት ነው:: ለዱዓ የሚያነሳሳም አላህ ነው:: አስታውሰህና ጊዜ ወስደህ እጅህን ከፍ አንድታደርግ ያደረገህ አሱ ነው:: አንዳንድ ሰው ቀደሩን ያውቅ ይመስል ዱዓ ኢድርጌ ቀደሬን ላልለዉጥ ነገር ምን አስለፋኝ ይላል:: ሰበብ ፈጥሮ ከዱዓ ይሳነፋል:: አላህን ከመለመን ይዘናጋል::

ወዳጄዋ! ቀደርህን ሳታውቅ ቢቃ ቀደሬ ነው አይቀየርም ብለህ ቁጭ ባልከበት አትሙት:: ይገርማል!! ሰው ሳይሞት እንዴት እጅ ይሠጣል!:: ሞኝ አትሁን ነገሮችን አላህ ነው የሻብኝ ብለህ አሥራቸው ቁጭ ብለህ አትደብደብ:: ሳትታሰር ታስሬያለሁ ብለህ ላለመንቀሳቀስ ምክንያት አትፍጠር:: በል አሁኑኑ ተነስ:: ከዚያ ካልወደድከው፣ ካደከመህና ካደቀቀህ ቀደር ወደዚያ ወደተሻለዉና ወደምትመኘው ቀደር ለመሸሽ ታገል:: ሰው ከማይሻለው ነገር ወደሚሻለው፣ ከከረምት ጨለማ ወደ ብራው ፀደይ፣ ከሐዘን እንጉርጉሮ ወደ ብሩህ ደስታ ለመሸሽ መሞከሩ አላህ የሻለትን ነገር አለመውድ ነው ማለት አይደለም:: ከመጥፎ ቀደርም ወደተሻለ ቀደር እንሸሻለን:: ከጥበትም ወደ ሰፋት፣ ከችግርም ወደ ድሎት እናማትራለን:: ቢድህነት ሙቱ ያለን የለም:: በበሽታ ማቅቁ ፈውስ አትፈልጉ አይባልም:: አላህ በሽታንም መድሃኒትንም ፈጠረ:: ሀብትንም ድህነትንም አሰገኘ:: መልካም ፀጋ ለመልካም ሙአሚን የተገባ ነው:: ፕንዙብ ቢያገኝ ይመፀዉታል:: ጤና ቢኖረው ደግ ይሠራበታል::

ወዳጆቼ! ሁሌም የተሻለዉን ነገር ተመኙ:: ታዲያ ይህ ሁሉ ሊሳካ የሚችለው በተለይ በሌሊት ሰዓታት በሚደረጉ ዱዓኦች፣ ሶላዋትና ኢስቲግፋር በማብዛት፣ ሱጁድ በማርዘምና አዝካሮች ላይ በማዘውተር ነው::

አላህ ሆይ! ያለንበትን ሁኔታ ወደተሻለ ሁኔታ ለውጥልን::